# የይሕዋ ምስክር አስተምህሮ

የእግዚአብሔር ቃል «ሁሉን መርምሩ መልካሙን ያዙ» (1ተሰ. 5፣21) በማለት ልንከተለው የሚገባ አምላካዊ ምክር ተሰጥቶናል። በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው ወይም የምንመረምረው የይህዋ ምስክር /JEHOVAH WITNESS/ እምነት ምን እንደሆነና በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሆን አለመሆኑን ነው።

## የይህዋ ምስክር
## መሠረታዊ እምነቶች ምንድን ናቸው?

1. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ነገር ግን ፍጡር እንጂ ከእግዚአብሔር አብ /JEHOVAH/ እኩል አምላክ አይደለም። በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ክርስቶስ ከፍጥረታት ሁሉ መጀመሪያ የተፈጠረ፤ ነገር ግን የአምላክነት ሥልጣን የተሰጠው ከእግዚአብሐር አብ በታች በሁለተኛ ደረጃ ያለ አምላክ ነው። የይህዋ ምስክር አማኞች ከክርስትና ሃይማኖት የሚለዩበት ከዋና ዋናዎቹ አንዱ ነጥብ ይሄ ነው።

## የእግዚአብሔር ቃል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ምን ይላል?

ኢየሱስ ክርስቶሰ ሥጋ ለብሶ ከመወለዱ በፊት የነበረውን መለኮታዊ ሥፍራ ከእግዚአብሔር ቃል እንመልከት። በፊልጵስዩስ 2፣6 ላይ «እርሱ /ክርስቶሰ/ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን (እኩል መሆንን) መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ» በማለት ኢየሱስ በሥጋ ከመገለጡ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሆኖ ይኖር እንደ ነበረና ለእኛ ሲል የሰውን መልክ እንደ ለበሰ በግልጽ ይነግረናል። በዮሐ. 10፣30-33 ደግሞ ኢየሱስ «እኔና አብ አንድ ነን» በሚልበት ጊዜ አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ እንዳነሡና ኢየሱስ «ከአባቴ ዘንድ በዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ ከእነርሱ ስለማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ?» ብሎ ሲጠይቃቸው ስለ መልካም ሥራ ሳይሆን «አንተ ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው

እንጂ» በማለት መለሱለት። ኢየሱስ እኔና አብ አንድ ነን ሲል ከአብ እኩል አምላክ ነኝ ማለቱ እንደሆነ ተረድተውት ነበረ ማለት ነው። በዮሐ. 14፣9 ላይ «እኔና ያየ አብን አይቷል» በማለት እርሱና አብ አንድ መሆናቸውን ደግሞ ያስረዳል። በዮሐ. 1፣1 እና14 ላይ ደግሞ ኢየሱስ በሥጋ ከመገለጹ በፊት እግዚአብሔር (አምላክ) እንደ ነበረ ያስረዳናል። «በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ»

## አልፋና ኦሜጋ ማነው?

በራዕ. 1፣8፤ 17-18 እና ራዕ. 22፣12-13፤ ላይ ኢየሱስ አልፋና ኦሜጋ የመጀመሪያውና የመጨረሻው አምላክ እንደሆነ በግልጽ ይናገራል። በቁጥር 8 ላይ «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፤ <u>አልፋና ኦሜጋ</u> እኔ ነኝ ይላል» የሚል ቃል እናነባለን። ይህ ጥቅስ ስለ ኢየሱስ ሳይሆን ስለ እግዚአብሔር አብ /JEHOVA/ ነው የሚናገረው የሚሉ አሉ፤ ነገር ግን የሚቀጥሉትን ጥቅሶች በምናነብበት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ይኸው የአምላክነት ስም በግልጽ ሲሰጠው እናያለን።

ቍጥር 17-18 «ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፤ አትፍራ <u>ፊተኛውና</u> (አልፋ) <u>መጨረሻው</u> (ኦሜጋ) ሕያው እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርኩ እነሆም <u>ከዘላለም እስከ ዘላለም</u> ድረስ ሕያው ነኝ፣» (ራዕ. 22፣12-13)።

«እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። <u>አልፋና ኦሜጋ</u>፣ <u>ፊተኛውና ኋለኛው</u>፣ <u>መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ</u>። ይላል። ከምዕራፍ ከምዕራፍ 1፣17-18 እና በምዕራፍ 22፣12-13 ያሉት ጥቅሶች የሚናገሩት ስለ ኢየሱስ አይደለም የምንል ከሆነ፣ ሞቶ የነበረው ማን ነው? ለእያንዳንዱ ዋጋውን ለመክፈል እንደገና የሚመጣውስ ማነው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ለማንም እውነተኛ ጠያቂ ግልጽ ነው። ተጨማሪ ማስረጃ ከፈለግን ግን ምዕራፍ 22፣16ትን ወረድ ብለን ብናነብ ሰለማን እንደሚናገር በግልጽ ይነግረናል። <u>«እኔ ኢየሱስ</u> በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይሀን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ።»

እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ፤ አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው መሆኑን በግልጽ ካስርዱን በምዕራፍ 1፣8 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር አብ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ካለ ኢየሱስ ክርስቶስና እግዚአብሔር እግዚአብሔር አብ /JEHOVA/ ሁለቱም አልፋና ኦሜጋ የሆኑ አንድ አምላክ ናቸው ማለት ነው:: ለዚህ ነው ኢየሱስ «እኔና አብ አንድ ነን» ያለው::

## ስግደት የሚገባው ለማን ብቻ ነው?

በማቴዎስ 4፣10 «ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ» የሚል ቃል እናነባለን:: በዕብራውያን ምዕራፍ 1:6 ላይ ደግሞ «የእግዚአብሔር ማላእክት ሁሉ ለእርሱ (ለክርስቶስ) ይስገዱ» የሚል ቃል እናነባለን:: ኢየሱስ ራሱ ፍጡር ከሆነ መላእክት ሁሉ እንዴት ሊሰግዱለት ይገባል? እንዴት ፍጡር ለፍጡር ይሰግዳል? መላእክቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ኢየሱስ በምድር ላይ ሲመላለስ ሰዎችም ይሰግዱለት እንደ ነበረ በበዙ ሥፍራዎች እናነባለን:: ነገር ግን በአንድም ቦታ «እኔ አምላክ ስላልሆንኩኝ አትስገዱልኝ፤ ስግደት የሚገባ አባቴ ብቻ ነው» /JEHOVA/ ብቻ ነው» ብሎ ሲከለክላቸው አናይም:: በአንፃሩ ደግሞ ቆርኔሌዎስ ለጴጥሮስ ሊሰግድለት ሲል እንደከለከለው በሐዋ. 10፣25-26 እናነባለን:: በራእ. 22፣8-9 ደግሞ ዮሐንስ በመልአኩ ፊት ሊሰግድ ሲደፋ «እንዳታደርገው ተጠንቀቅ» ብሎ እንደ ከለከለው እናነባለን::

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ጥቅሶች ለኢየሱስ የተደረጉትን ስግደቶች ያሳዩናል::

1 «ኮከቡን ከምሥራቅ አይተን <u>ልንሰግድለት</u> መጥተናል» ማቴ. 2፣2፤
2 «ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፣ <u>ወድቀውም ሰገዱለት::</u>» ማቴ. 2፣11
3 «እነሆም ለምጻም ቀርቦ፤ ጌታ ሆይ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ <u>ሰገደለት::</u>» ማቴ. 8፣2
4 «በታንኳይቱም የነበሩት፣ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው <u>ሰገዱለት</u>::» ማቴ.14፣33
5 እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት::» ማቴ. 28፣9
6 «/ሌጌዎን የነበሩበት ሰውዬ/ ኢየሱስን ባየ ጊዜ ሮጦ <u>ሰገደለት</u>::» ማር. 5፣6

7 «ቶማስም፤ <u>ጌታዬ፣ አምላኬም</u> ብሎ መለሰለት፡፡» ዮሐ. 20፣28
ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች እውነተኛ አንባቢ ለሆነ ሰው ሁሉ ስለ ኢየሱስ በግልጽ የሚናገርዋቸው ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም ነገሮች፤
ሀ. ኢየሱስ የሰዎችንና የመላዕክትን ስግደት እንደ ተቀበለ፤
ለ. ሊሰገድለት የሚገባው አንዱ አምላክ ብቻ ስለሆነ፤ ኢየሱስ ከአብ እኩል የሆነ አምላክ እንደሆነ፡፡

## ኢየሱስ፤ ፍጹም ሰው፡ ፍጹም አምላክ

ከላይ እንደ ጠቀስነው ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከሉን (አምላክነቱን) ትቶ ስለ ነበረ ሥጋን የለበሰው፤ እንደ ሰው መራብ፣ መጠማት፣ ወደ አባቱ መጸለይ ነበረበት፡፡ በፊል. 2፣6 እንደሚናገረው የሰውን ውስን ባህርይ ይዞ /የባሪያን መልክ ይዞ/ ስለ ነበረ «ከእኔ አብ ይበልጣል» ዮሐ. 14፣28 በማለት ፍጹም ሰው እንደ ነበረ ያስረዳናል፡፡ በንፃሩ ደግሞ ፍጹም አምላክም ስለ ነበረ «እኔና አብ አንድ ነን» «እኔን ያየ አብን አየ» በማለት የአምላክነቱን ባህርይ ያሳየናል፡፡ የይህዋ ምሰከረ አማኞች ፍጹም ሰውነቱን ብቻ በማየት ፍጹም አምላክነቱን እንዳያዩ ዓይናቸው የተጋረደ ይመስላል፡፡

የይህዋ ምስክር አማኞች የኢየሱስን አምላክነት ለሚያሳዩት ጥቅሶች የሚሰጡት መልስ ቢኖር እግዚአብሔር አብ ትልቁ አምላክ፣ ኢየሱስ ግን ትንሹ አምላክ ነው የሚል የማያጠግብ መልስ ነው፡፡ የእግዚአብሐር ቃል የትም ቦታ ቢሆን አንድ ትልቅ አምላክ ሌላ ደግሞ ትንሽ አምላክ አለ አይልም፡፡ ኢየሱስ አነስተኛ አምላክ ነው ለማለት የይህዋ ምስክር አማኞች ከሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች አንዱ ኢሳ. 9፣6 ነው፡፡
«... ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ /Mighty God/ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡» በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስን ኃያል አምላክ /Mighty God/ ሲለው በሌላ ቤታ እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል፣ ወይም ሁሉን የሚገዛ /Mighty God/ ይለዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢየሱስ አነስተኛ አምላክ መሆኑን ነው በማለት ይደመድማሉ፡፡ ነገር ግን በኢሳይያስ 10፣21 ላይ እግዚአብሔር አብ ኃያል አምላክ /Mighty God/ ይለዋል፡፡

# እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

«እግዚአብሔር አብ የክርስቶስ ነው» ሲል፣ ክርስቶስ ከእግዚአብሐር በታች መሆኑን ያሳየናል ይላሉ። የእግዚአብሔር ቃል «ቃሉ በሙላት ይኑርባችሁ» ስለሚል እነዚህን ጥቅሶች ለብቻቸው አውጥተን ወደ ውሳኔ ከመድረሰ ይልቅ ከሌሎች ጥቅሶች ጋር አብረን በምናስተያይበት ጊዜ የይህዋ ምስክሮች ትርጉሙ ሌላ ሆኖ እናገኘዋለን እግዚአብሐር አብ የክርስቶስ ራስ ነው ካለ በኋላ ወንድ ደግሞ የሴት ራስ ነው ይላል። በሌላ ቦታ ደግሞ ወንድ ወይም ሴት፣ ባሪያ ወይም ጨዋ የለም ሁሉም በክርስቶስ አን□ ነው ይላል። እነዚህን ጥቅሶች ላይ በምናይበት ጊዜ፣ «ወንድ የሴት ራስ ነው» ሲል ወንድ ከሴት ይበልጣል ለማለት ሳይሆን እግዚአብሔር የደነገገው የሥልጣን ተዋረድ /HIERARCHY/ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ወንድ ከሴት ስለሚበልጥ ሴት በግዴታ የወንድ ተገዥ ትሁን ማለቱ ሳይሆን ሴት ለወንድ በፍቅር ትገዛ /Submit/ ታድርግ ማለት ነው። እግዚአብሔር የክርስቶስ ነው ሲልም ክርስቶስ ከእግዚአብሔር እኩል አምላክ አይደለም ለማለት ሳይሆን ክርሰቶስ /ወልድ/ ራሱን ለእግዚአብሔር አብ በፍቅር እንዲስገዛ /Submition/ ሲያሳየን ነው።

# ኢየሱስ ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

የይሆዋ ምስክሮች ኢየሱስ ፍጡር ነው ለማለት የሚጠቀሙበት ጥቅስ ቈላ. 1፣15-16 ነው።

«...እርሱም (ኢየሱስ ክርስቶስ) የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ <u>በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና</u> ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል።» ቈላ. 1፣15-16። ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች እንደውም የኢየሱስን ፈጣሪነት እንጂ የኢየሱስን ፍጡርነት አያሳዩም። መጀመሪያ ኢየሱስ ፍጡር ነው ለማለት የሚጠቀሙበትን ክፍል እንመልከት። በዚህ ጥቅስ ላይ «ከፍጥረት

ሁሉ በፊት በኩር ነው» ሲል ከፍጥረት ሁሉ በፊት የነበረ አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው /ራእ. 22፣12-13/ እርሱ ነው ማለት እንጂ መጀመሪያ የተፈጠረው እርሱ ነው ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ኢየሱስ ራሱ ፍጡር ከሆነ ከፍጥረት ሁሉ በፊት የሚለው ቃል እርሱንም ስለሚያጠ ቃልል ከመፈጠሩም በፊት ነበረ ማለት ነው? ይህ አተረጓጎም ግራ የሚያጋባና እርሱ በርሱ የሚቃረን እንደሆነ ግልጽ ነው:: እንደውም እነዚህ ሁለት ጥቅሶች በተለይ ከዘፍ.1፣1 ጋር አብረን ስናስተያየው በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ ካለ፣ ምዕራፉን በሙለ በምናነብበት ገዜ ደግሞ ሰማይንና ምድርን ብቻ ሳይሆን በምድር የሚንቀሳቀሱትንና በሰማይ የሚበሩትን ሁሉ እግዚአብሔር ፈጠረ ካለ፣ በቈላስይስ ደግሞ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ /በክርስቶስ/ ተፈጥረዋል ካለ፤ ክርቶስ ሁሉን የፈጠረ አምላክ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ያደርሰናል::

## ኢየሱስ፤ የይሆዋ ምስክሮች እንደሚሉት ታናሽ አምላክ ነው ወይስ ታላቅ አምላክ?

ኢየሱስ ክርስቶሰ ታናሽ አምላክ ሳይሆን ታላቅና እውነተኛ አምላክ መሆኑን የሚያሳዩ ተጨማሪ ጥቅሶች አሉ::

«ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም <u>የታቁን የአምላካችንንና የመድኀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን</u> ክብር መገለጥ እየጠበቅን ... እንድንኖር ያስተምረናል::» ቲቶ 2፣13

«የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይዋት ነው::» 1ዮሐ. 5፣20::

## 2. ስለ መንፈስ ቅዱሰ

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ተንቀሳቃሽ ኃይል /Active Force/ እንጂ ህልውና /Personality/ ያለው አምላክ አይደለም ይላሉ::

ይህንንም አመለካከት ለመመርመር ጥቂት ጥያቄዎችን መጠየቅ በቂ ይሆናል፡፡

ሀ. መንፈስ ቅዱስ ህልውና የሌለው ኃይል ብቻ ከሆነ እንዴት ማዘን ይችላል?
«ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ ኤፌ. 4፣30፡፡

ለ. ሰው እንዴት ህልውና የሌለውን ነገር መዋሸት ይችላል?
«ጴጥሮስም፤ ሐናንያ ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ?

ሐ. ህልውና የሌለው ነገር እንዴት ፈቃድ ሊኖረው ይችላል?
«ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል፡፡ 1ቆር. 12፣11
«በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ፡፡ ሐዋ. 16፣6፡፡

መ. ህልውና የሌለው ኀይል እንዴት ይናገራል?
«እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ፣ መንፈስ ቅዱስ፤ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡» ሐዋ. 13፣12፤
«መንፈስም ፊልጶስን፤ ወደዚህ ሰረገላ ቅርብና ተናኝ ሐዋ. 8፣29

ሠ. ህልውና የሌለው ኃይል እንዴት መማለድ ይችላል? «እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድልንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፣ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፡፡» ሮሜ 8፣26

ረ. ህልውና የሌለው ነገር እንዴት «እርሱ የሚል ተውላጠ ስም ይሰጠዋል?
«እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንደሄድ ይሻላችኋለሁ፡፡ እኔ ባልሄድ ግን አጽናኙ ወደ እናንተ አይምጣና እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ፡፡ እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፡፡» ዮሐ. 16፣7-8

ሌሎችም ብዙ ጥቅሶችን መጥቀስ ይቻላል፤ ነገር ግን ስለ መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው መንፈስ ቅዱስ ህልውና የሌለው ኀይል ብቻ አለመሆኑን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች በቂ ማስረጃ ናቸው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ህልውና ያለው፤ የሚያዝን፣ የሚናገር፣ የሚፈቅድና የሚከለክል፣ የሚማልድ፣ ወዘተ... ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ማነው?

በሐዋ 5፣3 ላይ ጴጥሮስ ሐናንያ «መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ? ካለው በኋላ በቁጥር 4 ላይ «እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም» ይለዋል። ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው።

## 3. ስለ ሥላሴዎች

የይህዋ ምስክር አማኞች፤ ሥላሴ የሚለው ቃልም ሆነ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ የስህተት ትምህርት ነው ይላሉ።

ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖር አለመኖሩ ሳይሆን፤ «አብ፣ ወልድና፣ መንፈስ ቅዱስ በአንዱ አምላክ /Godhead/ ውስጥ ያሉ፣ ሦስቱም እኩል የሆኑ እግዚአብሔር ናቸው» የሚለው የሥላሴ ትምህርት የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ ላይ ነው ማተኮር ያለብን።

## አንድ አምላክ በሦስት መልክ ተገለጸ ስንል ምን ማለታችን ነው

በዘፍ. 1፣26 «እግዚአብሔር አለ፣ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር...» የሚለውን ቃል በምናነብበት ጊዜ ፍጡር የሆነ ነገር መፍጠር ስለማይችል፤ እግዚአብሔር «እንፍጠር» በሚልበት ጊዜ እንደ እርሱ የፈጣሪነት ባህርይ ያላቸው ግለሰቦችን / Personalities/ መሆን አለበት።

አብ ፈጣሪ እንደ ሆነ በዘፍ. 1፣1 ላይ እንመለከታለን «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።»

ወልድ (ክርስቶስ) ፈጣሪ እንደሆነ በቈላ. 1፣15-16 እንመለከታልን፤ «እርሱም (ኢየሱስ ክርስቶስ) የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያለት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በኵር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ

ተፈጥሮአል፡፡»

<u>መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በፍጥረት ጊዜ ተባባሪ እንደ ነበረ</u> ከዘፍ. 1፣2 እናነባለን «የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር፡፡» በተጨማሪም በመዝ. 104፣30 መንፈስ ቅዱስ በፍጥረት ሥራ ውስጥ እንደሚሳተፍ እናነባለን፡፡ <u>«መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠ ራሉም</u>፣ የምድርን ፊት ታድሳለህ፡፡»

የሥላሴን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚደግፈው ከመመልከታችን በፊት መጀመሪያ በአንድ ሐሳብ እንስማማ፤ ይህም ሐሳብ፣ ሦስት ነገሮች ከአንድ ነገር ጋር እኩል ከሆኑ እርስ በርሳቸውም እኩል ናቸው ማለት ነው፡፡ በእግዚአበሔር ቃል ውስጥ <u>አብ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ ወልድ እግዚአብሐር እንደሆነ፣ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር እንደሆነ</u> ካረጋገጥን፤ የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ቦታዎች አንድ እግዚአብሐር ብቻ አለ ስለሚል፤ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ናቸው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ሦስቱም በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ካለ፤ ሦስቱም በአንድነት ሆነው ያን አንዱን እግዚአብሔር ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

## እግዚአብሔር አብ

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ <u>አብ እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይናገራል፡፡</u> «ከገናናው ክብር፤ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምፅ በመጣለት ጊዜ <u>ከእግዚአብሔር አብ</u> ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤» 2ጴጥ. 1፣17፡፡

## እግዚአብሐር ወልድ

<u>ወልድ እግዚአብሔር እንደሆነ</u> እነዚህ ጥቅሶች ይናገራሉ፤

«ይህም ጸጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም <u>የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን</u> ክብር መገለጥ እይጠበቅን... እንድንኖር ያስተምረናል፡፡» ቲቶ 2፣13፡፡

«የእግዚአብሐርም ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፣ እርሱም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርሱም እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው፡፡» 1ዮሐ. 5፣20፡፡

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም ሥጋም ሆነ።» ዮሐ. 1፣1-14።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ይናገራል።

«ጴጥሮስም፤ ሐናንያ ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ?.. እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም።» ሐዋ. 5፣3-4።

አንድ አምላክ

ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ሦስትነታቸውን ስናይ በሚቀጥለው ጥቅስ ደግሞ አንድነታቸውን እናያለን።

«እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።» ኦሪት ዘዳግም 6፣4።

እነዚህን ጥቅሶች በአንድነት በምንመለከትበት ጊዜ፤ አብ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ ወልድ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ሆነ፤ በአጠቃላይ ደግሞ አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንዳለ እናያለን። የሥላሴ ትምህርትም ይህንኑ ነው የሚያስተምረው። አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ። ይህንን ትምህርት የበለጠ ለአምሮአችን እንዲገባን ለማድረግ በየቀኑ የምንጠቀምበትን የውኃን ባህርይ ማየት እንችላለን። የውኃ ሙቀት ከተወሰነ ዲግሪ በታች በሚሆንበት ጊዜ በረዶ ይሆናል ከተወሰነ ዲግሪ በላይ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ እንፋሎት ይሆናል። መሀከለኛ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ፈሳሽ ውኃ ይሆናል። ፍጡር የሆነው ውኃ ባህርዩን በሦስት መንገድ መግለጽ ከቻለ፣ ውኃን የፈጠረ አምላክ በሦስት መንገድ ቢገለጽ ምን ያስደንቃል?

## 4. ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ ራሳቸውን የሾሙ ነቢያት፤

የይህዋ ምስክር ዋና ማዕከላዊ ድርጅት /THE WATCHTOWER/ በዚህ ዘመን የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰዎች የምናመጣ ነቢያቶች እኛ ነን በማለት ይናገራል። የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛውንና ሐሰተኛውን ነቢይ የምንለይበትን መንገድ በዘዳግም 18፣21-22 አሳይቶናል። «በልብህም፣ እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፤ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።» በማቴዎስ 7፣15-16 ደግሞ «የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ። ከፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?» በማለት መጠንቀቅ እንዳለብን ያሳስበናል። ራሱን እንደ ነቢይ አድርጎ የሚቆጥረው የይህዋ ምስክር መሪዎች ጉባኤ /THE WATCHTOWER ባለፉት ዘመናት ብዙ ይሆናሉ ብሎ የተነበያቸው ትንቢቶች ነበሩ።

## ትንቢቶቻቸውን በጥቂቱ እንመልከት

JAN. 1886 (እ.ኤ.አ) ባወጡት ጽሑፋቸው ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በ1914 (እ.ኤ.አ) መጥቶ የዓለምን መንግሥታት ድል እንደሚያደርግና መንግሥቱን እንደሚመሠርት ተናግረው ነበረ። በ1918 ደግሞ በብሉይ ኪዳን የነበሩት የእግዚአብሔር ነቢያት አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና በተለይም በዕብራዊያን 11 ላይ ያሉት የእምነት አባቶች በ1925 በገሃድ እንደሚገልጹ ተንብየው ነበረ። በመጽሔታቸው ላይ ቃል በቃል። በመጽሔታቸው ላይ ቃል በቃል "Therefore we may confidently expect that 1925 will mark the return of Abraham, Isaac, Jacob and the faithful prophets of old, particularly those named by the Apostle in Hebrews 11, to the condition of human perfection." MILLION NOW LIVING WILL NEVER DIE, page 89.

በ1931 ባወጡት እትም ላይ የክርስቶስ የሺህ ዓመት ንግሥ የሚጀምረው በ1975 ነው በማለት ሌላ ትንቢት ተንብየው ነበረ።

ይህንኑ ትንቢት በማጠናከር በ May 1974 እንደ እነርሱ ትንቢት የዓለም መጨረሻ ጥቂት ወራት ሲቀረው HOW ARE YOU USING YOUR LIFE /ሕይወትህን እንዴት ነው የምትጠቀምበት?/ በሚል አርእስት ባወጡት ጽሑፍ ላይ፤ የዚህ የክፉ ዓለም መጨረሻ ስለ ደረሰ አንዳንድ ወንድሞች ያላቸውን ሃብትና ንብረት ሸጠው የመንግሥቱን ወንጌል ለማስፋፋት እየተጠ ቀሙበት እንደሆነ፣ ይህም መልካም አርአያነት እንደ ሆነ ገልጸው ነበረ። እነዚህን ሁሉ ትንቢቶች በምንመለከትበት ጊዜ አንዱም እውነት ሆኖ አናገኘውም። በተጨማሪም የይሆዋ ምስክር የእግዚአብሔርን ቃል ለራሳቸው እንደሚያመች ሲለዋውጡት እናያለን፤ ይህም በአዲሱ የእንግሊዝኛ እትም መጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ በግልጽ ይታያል። በዮሐ. 1፣1 ላይ 'The word was God" የሚለውን "The word was god" በማለት የክርስቶስን አምላክነት ዝቅ እንዳደረጉት እናነባለን።

የሥላሴ እምነት ሦስት አማልክት አሉ ሳይሆን አንዱ አምላክ በሦስት መልክ /Three persons/ እንደ ተገለጸ ነው የሚያስተምረን።

## በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ

ምናልባት በዚህ በይህዋ ምስክር እምነት ውስጥ የምንገኝ በእግዚአብሔር ቃል ራሳችን መመርመር ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቃል፤ «ሰው ሁሉ ውሸተኛ ቢሆን እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።» /ሮሜ 3፣4/ እንደሚለው ከሰው ያገኘነው ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ሲታይ ውሸት ሆኖ ሊገኝ ይችላል፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም እውነት ሆኖ ይኖራል። የይህዋ ምስክር እንደሚያስተምረው ፍጡር የሆነውን ኢየሱስ ሳይሆን የሁሉ ፈጣሪና እውነተኛ አምላክ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ወደ ልብህ ተቀበለው። «እነሆ በደጄ ቆሜ አንኳኳለሁ፡ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ» በማለት የልብህን በር ያንኳኳል። ልብህን መክፈቱና ወደ ሕይወትህ መጋበዙ ያንተ ፈንታ ነው።

## ፈቃደኛ ከሆንክ ይህንን ጸሎት ከልብህ ጸልይ

«ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! አንተ ፍጡር ሳትሆን እውነተኛ አምላክና የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ መሆንህን አምናለሁ፡፡ ስለ እኔ ኃጢአት ብለህ ደምህን እንዳፈሰስህልኝ አምናለሁ፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ የሠራሁትን ኃጢአት በሙሉ ይቅር በለኝ፡፡ ወደ ልቤ እንድትገባ የልቤን በር ከፍቼ እጋብዝሃለሁ፡፡ የሕይወቴ አዳኝና ጌታ አድርጌ እቀበልሃለሁ፡፡ ከዛሬ ጀምሮ በእውነት መንገድ ምራኝ፡፡ ከቃልህ እውነትህን አስተምረኝ፡፡ በዮሐ. 1፥12 መሠረት ልጅህ አድርገህ ስለተቀበልከኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሜን»

«ለተቀበሉት ሁሉ በስሙ ለሚያምኑት የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፡፡» ዩሐ. 1፥12

ከላይ ያለውን ጸሎት ከጸለይህ ተጨማሪ መንፈሳዊ ጽሑፍ እንድንልክልህ በአድራሻችን ብትጽፍልን ደስ ይለናል፡፡

GLOBAL GOOD NEWS LITRATUE
P.O.BOX 451336
LOSANGELES CA 90045